# ጥናት አንድ ማቴ 4፡12-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ በገሊላ ወደ ምትገኘው ወደ ቅፍርናሆም ከመምጣቱ በፊት ቁ13 እንደሚነግረን ይኖር የነበረው በናዝሬት ከተማ ነበረ። ናዝሬትን ትቶ ወደ ገሊላ በመምጣት አገልግሎቱን የጀመረበት ምክንያት በቁ14-16 ከምናነበው በኢሳያስ በኩል የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው።
2. እግዚአብሄር አንዳንድ ነገሮችን ለምን እንደሚያደርግ በጊዜው ባይገልጥልንም እንኳን፤ ከዚህ ሁኔታ እንደናየው ኢየሱስ ዮሐንስን በመተካቱ ለህዝቡ የተሻለን ነገር እንዳየለት መረዳት ይቻላል። እጅግ የምንወዳቸውና የምናከብራቸው ታማኝ የጌታ አገልጋዮች በተለያየ መንገድ ከመካከላችን ሲለዩ፤ እግዚአብሄር በተሻሉ አገልጋዮች ሊባርከን እንደሚችል ማመን እንዲኖርብን ያስተምረናል።
3. ይህችን ከተማና በውስጧ የሚኖረውን ህዝብ ኢሳያስ የሚገልጣት፤ የአህዛብ ሃገር እንደሆነች፣ ህዝቧ በጨለማ የሚኖር እንደሆነና፤ ምድሪቱ የሞት ጥላ ያጠላባት እንደነበረች አድርጎ ነው። ይህች ከተማና ነዋሪዎቿ ከጨለማ ወጥተው ብርሃን ማየት የቻሉት ከኢየሱስ መምጣት የተነሳ እንደሆነ ከትንቢቱ መገንዘብ ይቻላል።
4. ፀሐፊው ‹‹ከዚያን ጊዜ አንስቶ›› ሲል ዮሐንስ የታሰረበትን ጊዜ ሊጠቁመን እንደፈለገ እረዳለሁ፡ ይህ ጊዜ የእግዚአብሄር መንግሥት እንደቀረበ፣ ሰዎችም ንስሃ መግባት እንደሚኖርባቸው ያስጠነቅቅ የነበረው የመንገድ ጠራጊው ድምጽ በመታፈኑ፤ ኢየሱስ ዮሐንስ የጀመረውን የንስሃ ጥሪ ድምጽ ማስተጋባት መጀመሩ ለእርሱ አገልግሎቱን በግላጭ የጀመረበት ጊዜ አድርገን መውሰድ እንደምንችል እረዳለሁ ነው።
5. እነዚህ ሁለት ሰዎች ወንድማማቾች ናቸው፣ ሁለቱንም ኢየሱስ አያቸው፣ ሁለቱም አሳ አጥማጆች ነበሩ፣ ሁለቱም መረባቸውን ወደ ባህር ይጥሉ ነበር፣ ለሁለቱም በአንድ ቀን ከኢየሱስ የመከተል ጥሪ ደረሳቸው፣ ሁለቱም መረባቸውን ትተው ተከተሉት።
6. በቁ21-22 ውስጥ የተጠሩት ሰዎች ያዕቆብና ዮሐንስ ናቸው። በቁ18-21 እባ በቁ21-22 የተካሄዱትን ጥሪዎች ስናነጻጽር፤ ተመሳሳይነታቸው፡ በሁለቱም ክፍሎች የተጠሩት ወንድማማቾች ናቸው፣ ሁለቱም በአሳ አጥማጅነት ሥራ የተሰማሩ ነበሩ፤ ሁለቱም ሲጠሩ ወዲያው ነው የተከተሉት፤ ልዩነታቸው ደግሞ፡ አንዳቸው መረባቸውን ሲጥሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ መረባቸውን ያበጁ ነበረ፣ የመጀመሪያዎቹ ጥሪው ከነምክንያቱ የተነገራቸው ሲሆን፣ ሁለተኛዎቹ ጥሪ ብቻ ነው የቀረበላቸው፣ እነ ስምዖን ብቻቸውን ሲሆኑ፣ እነ ያዕቆብ ከአባታቸው ጋራ ነበሩ፤ እነስምዖን መረባቸውን ትተው ተከተሉት፣ እነ ያዕቆብ ጀልባቸውንና አባታቸውን ትተው ተከተሉት። ይህ ክፍል ኢየሱስ ከቤተሰብ፣ ከስራችንና ካለን ሃብት ሁሉ መቅደም እንደሚኖርበት ያስተምረናል።
7. መጀመሪያ መቅደም የሚኖርበት ነገር ኢየሱስን መከተል ሲሆን፣ ግብ ተደርጎ የተነገረው ደግሞ ሰዎችን አጥማጅ ለመሆን መብቃት የሚለው ሃሳብ ነው። በዚህ ውስጥ የኢየሱስ ሚና ሆኖ የማየው፤ ‹‹አደርጋችኋለሁ›› የሚለው አነጋገር ኢየሱስ የሚከተሉትን ሰዎች ህይወት እንደሚሰራና ወደሚፈልግበት ደረጃ እንደሚያመጣ እረዳለሁ።
8. እነዚህ ሶስት ነገሮች ብዬ የማያቸው 1) ኢየሱስን መከተል 2) ኢየሱስ የተከታዮቹን ህይወት መስራትና መለወጥ 3) ሰዎችን አጥማጅ ለመሆን መብቃት የሚሉትን አያለሁ።

# ጥናት ሁለት ዮሐ 6፡48-71 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጎልቶ በዚህ ክፍል የሚታየው ቃል ‹‹እንጀራ›› የሚለው ቃል ነው፡፡ ኢየሱስ ራሱን ሲያወዳድር የምናየው በምድረበዳ ከወረደው መና ጋራ ነው፡፡ እነዚህ ምግቦች ሁለቱም ከሰማይ የወረዱ መሆናቸው ሲያመሳስላቸው፤ በሌላ በኩል ግን፤ መናውን የተመገቡት ሰዎች ሁሉ ተመልሰው የሞቱ ሲሆን፣ ኢየሱስን የሚበላ ሰው ግን ለዘለዓለም መኖሩ ልዩነታቸውን በጉልህ ያመለክተናል፡፡
2. ኢየሱስ ይህንን ሃሳብ አስረግጦ እንዲናገር ምክንያት ከሆኑት ነገሮች አንዱ፤ በቁ52 ላይ አይሁዶች እርስ በእርሳቸው ይከራከሩበት ለነበረው ሃሳብ መልስ ለመስጠት ይመስለኛል፡፡ ጌታ የሱስ ሥጋውን ስለመብላትና ደሙን ስለመጠጣት ሲናገር፤ ቁ47ትንና ቁ54ትን ብናስተያይ ‹‹የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት አለው፡፡›› በማለት በቁ54 ላይ ደግሞ ‹‹ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ህይወት አለው›› ሲል ሥጋውን መብላትና ደሙን መጠጣት ማለት በእርሱ ማመን ማለት እንደሆነ እንረዳለን፡፡
3. የዘላለም ህይወት አለው፣ አስነሳዋለሁ፣ በኢየሱስ ውስጥ ይኖራል፣ ኢየሱስ በእርሱ ውስጥ ይኖራል፣ በህይወት ይኖራል፣ ለዘለዓለም ይኖራል፡፡ እነዚህ ሰዎች ለጥያቄያቸው መልስ ቢሰጣቸውም፣ የተሰጣቸውን መልስ በትክክል ካለመረዳታቸው የተነሳ ወደበለጠ ጥያቄ የከተታቸው እንጂ መልስ የሆነላቸው አይመስለኝም፤ ይህንን ያልኩበት ምክንያት በቁ60 ላይ ደቀ መዛሙርቱ ከተናገሩት ንግግር በመነሳት ነው፡፡
4. ደቀመዛሙርቱ ይህንን በማለት የተናገሩበት ምክንያት ለእኔ እንደገባኝ፤ የሰውን ሥጋና ደም መብላት በማናቸውም ማህበረ ሰብ ውስጥ ቢሆን ተቀባይነት የሌለው ነገር በመሆኑ፤ እነዚህ ሰዎች ነገሮችን ሲሰሙሙም ሆነ መረዳታቸው በሥጋዊ አንጻር በመሆኑ፤ መንፈሳዊ ትርጉም እንዳለው ማስተዋልና መረዳት ስላልቻሉ እንደሆነ አገምታለሁ፡፡
5. ቁ61 እንደሚነግረን ማጉረምረማቸውን ለኢየሱስ ማንም የነገረው እንዳልነበረና ሁኔታውን ያወቀው በራሱ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህ ሁኔታ ሊያስተምረን የሚችለው ነገር፤ ኢየሱስ እርሱ የሰዎችን ልብና ሃሳብ የሚያውቅ አምላክ እንደሆነና ሰዎች ሊነግሩት እንደማያስፈልገው ማየት እንችላለን፡፡
6. ኢየሱስ ይህንን የተናገራቸው ሰዎች በቁ61 ላይ ያሉት ደቀመዛሙርት ተብለው ለተጠሩት ሰዎች ነው፡፡ አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳ በዚህ ክፍል የተመደበው ካላመኑት ሰዎች ጋራ ነው፡፡ የኢየሱስ ደቀመዝሙር መባል፣ ለብዙ ጊዜ ከእርሱ ጋራ መመላለስና፣ እርሱን ማገልገል ለሰዎች የደህንነታቸው ማረጋገጫ ሊሆን እንደማይችል እመለከታለሁ፡፡
7. አስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት እንዲመልሱት የቀረበላቸው ጥያቄ፤ እነርሱም እንደሌሎቹ ኢየሱስን ተተው እንደሄዱት ሰዎች መሄድ እንደሚፈልጉ ነበረ፡፡ ከኢየሱስ መለየት እንደማይፈልጉ ጴጥሮስ የሰጣቸው ሁለት ምክንያት፤ አንደኛው ኢየሱስ የዘለዓለም የህይወት ቃል ስላለው፣ ሁለተኛው ደግሞ ኢየሱስ ብቻውን የእግዚአብሄር ቅዱስ እንደሆነ ስላወቁና ስላመኑ ነው፡፡
8. ኢየሱስ ሰዎች ሊሰሙ የሚፈልጉትን ብቻ እየተናገረ ከእርሱ ጋራ የማቆየት ፍላጎት ላይ የተመሰረተ አገልግሎት ሳይሆን፤ ቁ65 እንደሚናገረው አባቱ የሳበው ሰው ወደ እርሱ እንደሚመጣ ተረድቶ እውነትን ሳይበርዝ መናገር ስለቆረጠ ነው፡፡ ጴጥሮስ ይህንን ሲል ሌላ መሄጃ ወይም ሰርተን መብላት የምችሉበት መንገድ እንደሌለ ማስታወቁ ሳይሆን፤ አንድ ጊዜ የኢየሱስን ማንነት ከተረዱና የህይወት ትርጉም የሆነውን የእግዚአብሄር ልጅ ካገኙ በኂላ ወደሌላ አቅጣጫ ፊትን ማዞር የማያዋጣ ነገር መሆኑን መናገሩ ይመስለኛል፡፡

## ጥናት ሶስት ማቴ 14፡22-36 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ከዚህ ክፍል አስቀድሞ ኢየሱስ ሴቶችንና ህጻናትን ሳይጨምር አምስት ሺህ ወንዶችን በአምስት እንጀራና በሁለት አሳ መግቦ አስራ ሁለት መሶቦች የተረፉበት ተአምራት እንደተከናወነ እናነባለን፡፡ ኢየሱስ ካደረገው ተአምራት የተነሳ ወደ ዓለም የሚመጣው ነብይ ብለው ኢየሱስን በግድ ለማንገስ እንደፈለጉ ዮሐንስ ይናገራል፡፡
2. ደቀ መዛሙርቱንና ህዝቡን ካሰናበተ በኂላ ኢየሱስ ያደረገው ነገር ብቻውን ለመጸለይ ወደ ተራራ እንደወጣ እናያለን፡፡ በእኔ አመለካከት እግዚአብሄር ይህንን ያህል ህዝብ ለመመገብ ተአምራት ለማድረግ በመፍቀዱ የምስጋና ጸሎትና በሌላ በኩል ደግሞ ዮሐንስ 6፡14-15 ላይ ከተናገረው አንጻር ህዝቡ ከፍ ከፍ ማድረግ መጀመራቸው ከተልዕኮው ፈቀቅ እንዳያደርገው አባቱን የሚለምንበት ሊሆን ይችላል እላለሁ፡፡
3. በእኛም ህይወት እግዚአብሄር እንድናደርግና እንድንሰራ በሰጠን ሃላፊነት ውስጥ ሁልጊዜ ነገሮች ያለምንም ተቃውሞና ተግዳሮት መሄድ አለባቸው የሚለው አመለካከት ትክክል እንዳልሆነና፣ ነገሮች አንዳንድ ጊዜ እኛን እንኳን ለአደጋ ለመዳረግ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል መቀበል ይኖርብናል፡፡ ችግር ደረሰብን ማለትም ሁልጊዜ ከእግዚአብሄር ሃሳብና ፈቃድ ውጭ ነን ማለት ላይሆን ይችላል፡፡
4. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናየው ነገር ኢየሱስ በውሃ ላይ እየተራመደ ሲሄድና፣ ደቀ መዛሙርቱ ደግሞ ይህንን ሁኔታ ሲያዩ ምትሃት እንደሆነ በማሰብ ፈርተው ሲጮሁ እንመለከታለን፡፡ እነዚህ ሰዎች ሁኔታውን ከምትሃት ጋራ ያያያዙትና የፈሩበት ምክንያት በተለይም አሳ አጥማጆች እንደመሆናቸው ኑሯቸው ከውሃ ጋራ የተቆራኘ ሆኖ አንድም ሰው ከዚህ በፊት በውሃ ላይ ሲሄድ አይተው ስለማያውቁ ከዚያ የተነሳ ነው ወደዚህ አይነቱ አነጋገር የደረሱት ብዬ አምናለሁ፡፡
5. የመጀመሪያው ሁኔታ የጀልባቸው በነፋስና በማዕበል ውስጥ ሆኖ መንገላታታቸው ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ አይተው የማያውቁትና አስፈሪ የሆነባቸው ምትሃት ብለው ያሰቡት ሁኔታ ነው፡፡ የኢየሱስ መገለጥና እንዳይፈሩ ማበረታታቱ፣ በአንደኛ ደረጃ ምትሃት የሚለው ጥያቄ የሚወገድ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እርሱ ነፋሱና ማዕበሉን የሚያዝ ጌታ ስለሆነ ለሁለተኛውም ችግራቸው መፍትሄ ይሆንላቸዋል ማለት ነው፡፡
6. የኢየሱስ በመሃላቸው መገኘት ምናልባትም ደቀ መዛሙርቱ በሙሉ ደስ የተሰኙበት ነገር ቢሆንም እንኳን፣ ለጴጥሮስ ግን አዲስን ነገር የመለማመድና በኢየሱስ ላይ ያለውን እምነት ማዳበሪያ አድርጎ የሚያይበት ሁኔታና እድል አድርጎ ተጠቅሞበታል ማለት እንችላለን፡፡
7. ቁ33 ላይ የምናነበው በጀልባው ውስጥ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ በእውነትም የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ በልባቸው ያረጋገጡበት ነገር መሆኑን፣ ስለዚህም ለእርሱ እንደሰገዱለት እናነባለን፡፡
8. ጴጥሮስ ሊሰጥም እንደሚጀምር ኢየሱስ አስቀድሞ የሚያውቅ ቢሆንም፣ በውሃው ላይ ተራምዶ ወደ እርሱ እንዲመጣ የፈቀደለት ምክንያት፣ ለመስጠም በመጀመርም እንኳን ቢሆን የደቀ መዝሙር እምነት በኢየሱስ ላይ እንዲያድግና እንዲዳብር ፍላጎቱና አላማው ስለሆነ ነው፡፡

# ጥናት አራት ማቴ 15፡1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ፣ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት፣ ፈሪሳውያንና የኦሪት ህግ መምህራን፣ በቁ10 ሕዝቡ በመባል የተጠቀሱት (ማቴ 14፡35 ላይ የጌንሴሬጥ ነዋሪዎች የሚላቸው)፡፡ የፈሪሳውያኑ ጥያቄ ያተኮረው በአባቶች ወግና እጅን በመታጠብ ባለመታጠብ ላይ ነበረ፡፡ ኢየሱስ ትኩረታቸውን ከወግ ላይ አንስቶ ወደ እግዚአብሄር ትዕዛዝና ህግ ላይ ሲመልሰው እንመለከታለን፡፡
2. የነዚህ ፈሪሳውያን ጥፋት ለወግና ለሥርዓታቸው ከእግዚአብሄር ህግና ትዕዛዝ በላይ በማድረግ ሥፍራ መስጠታቸው ነው፡፡ በዚህ ስፍራ በምሳሌነት የቀረበው አባትና እናትህን አክብር የሚለው በዘፀ 20፡12 እና በዘፀ 21፡17 የተነገረው ቃል ሲሆን፣ የእነርሱ ወግ ደግሞ አባት እናትን ማክበር የሚለውን ሃሳብ በቁ5 ላይ በምናየው መንገድ የተቀየረና የተሻሻለ ነው፡፡
3. በዚህ ቦታ አባትህንና እናትህን አክብር የሚለው ሃሳብ እነርሱን በሚያስፈልጋቸው ነገር የመርዳትና የመደገፍን ነገር ነው የሚያመለክተን፡፡ ይህ አይነቱን የኢየሱስ ትርጉም ስንመለከት 1ኛ ጢሞ 5፡17 ላይም የሰፈረው ክብር የሚለው ሃሳብ ምናልባትም ይህንን በዚህ ስፍራ ያነበብነውን አይነት በገንዘብና በተለያየ መንገድ ድጋፍ የመስጠትን ነገር ያጠቃልላል ብዮ አስባለሁ፡፡
4. ምክንያቱም ገንዘብንም ሆነ ሌላ ንብረት ለእግዚአብሄር ቤት መባ አድርጎ ማምጣት መልካም ነገር ቢሆንም፣ በዚህ ሥፍራ የምንመለከተው እግዚአብሄርን በግልጽ ያዘዘውን ትዕዛዝ በመጣስ በራሳቸውን አስተሳሰብ የተሸለ ሆኖ ያዩትን ነገር ለማድረግ መወሰን በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት የለውም፤ የእግዚአብሄር ቃል በ1ኛ ሳሙ 15፡22 እንደሚናገረው መታዘዝ ከመስዋዕት ይበልጣልና ነው፡፡
5. ኢሳያስ የሚናገረው እነዚህ ሰዎች በከንፈራቸው ብቻ እግዚአብሄርን እንደሚያከብሩ፤ ልባቸው ግን ከእርሱ የራቀ እንደሆነ፤ እግዚአብሄርን በከንቱ ያመልኩታል፤ ትምህርታቸው ሁሉ ግን የሰው ሥርዓት ነው፡፡ ኢየሱስ ለነዚህ ዓይነት ሰዎች የሰጠው ስም ‹‹ግብዞች›› የሚል ነው፡፡
6. ኢየሱስ ህዝቡን የሚነግራቸው እንዲሰሙና እንዲያስተውሉ ነው፡፡ እንዲሰሙና እንዲያስተውሉ የፈለገውም ነገር፤ ፈሪሳውያኑ በቁ2 ላይ ለጠየቁት ጥያቄ ምላሽ የሚሆነውን ከአፍ የሚወጣ እንጂ ወደ አፍ የሚገባ እንደማያረክስ ያስተማረውን ትምህርቱን ነው፡፡ በፈሪሳውያኑ መቆጣት ያልተገረመው፤ በመጀመሪያ ደረጃ አብ ያልተከለው ተክል ስለሚነቀል፤ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ሰዎች ዕውር መሪዎች እንደሆኑና አመራራቸውም ወደገደል የሚወስድ እንደሆነ ስለሚያውቅ መሆኑን ቁ13-14 ይነግረናል፡፡
7. ኢየሱስ የጠየቃቸው ‹‹እናንተም እስካሁን አላስተዋላችሁም ማለት ነውን?›› በማለት ነው፡፡ እንደ ኢየሱስ አነጋገር ከሆነ ሰዎች የበለጠ ጥንቃቄ ሊያደርጉ የሚገባቸው ወደአፋቸው ከሚገባው ነገር ይልቅ ከአፋቸው ለሚወጣው ነገር መሆኑን በግልጽ እንረዳለን፡፡ ከአፍ የሚወጣው ሰውን ስለማርከሱ ኢየሱስ ምክንያት አድርጎ የሰጠው ነገር፤ ከአፍ የሚወጣው ከልብ ስለሚመነጭ ነው፤ የሰው ለብ ደግሞ እጅግ ክፉ እንደሆነ በሌላ ሥፍራ ተነግሮናል፡፡
8. ለደቀመዛሙርቱ ሁሉ ያለማወቃቸው መጋለጥ ምክንያት የሆነው ሰው ጴጥሮስ ነው፡፡ ጴጥሮስ ያልገባውን ነገር እንደገባው ሆኖ ዝም ቢል ኖሮ፤ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ኢየሱስ በቁ17-20 ላይ ያስተማራቸው ትምህርት ሳያገኙ ይቀርባቸው እንደነበረ እገምታለሁ፡፡

# ጥናት አምስት ማቴ 18:21-35 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ21 ላይ የጴጥሮስ ጥያቄ የመነጨው፤ በቁ15-17 ላይ ኢየሱስ በተለይ በቁ15 ላይ ‹‹ወንድምህ ቢበድልህ›› በማለት ግጭት በምን መንገድ ሊፈታ እንደሚገባው ከተናገረው ንግግር በመነሳት ነው። ‹‹ወንድሜ ቢበድለኝ›› የሚለው አነጋገር ሁልጊዜ እንደምናስበው ሌላው በዳይ እኛ ተበዳይ እንዳይሆን፤ ‹‹ወንድሜን ብበድለው ስንት ጊዜ ይቅር ይበለኝ?›› በማለት ለመጠየቅ ይችል እንደነበረ አስባለሁ።
2. ጴጥሮስ ከእጥፍ በላይ ከፍ አድርጎ ሰባት ጊዜ ማለቱ ኢየሱስ ያለ ምንም ጥርጥር እንደሚያጸድቅለት የጠበቀ ይመስለኛል። በመጀመሪያ ደረጃ 490 ጊዜ በደልን ለመከታተልና ለመቁጠር ለእያንዳንዱ ሰው ማስታወሻ ደብተር ማዘጋጀት ያስፈልጋል ማለት ነው፤ እኔ እንደምረዳው ኢየሱስ ሊያስተምራቸው የፈለገው ትምህርት ለይቅርታ ገደብ አታብጁለት የሚል ይመስለኛል።
3. መንግሥተ ሰማይ ‹‹በአገልጋዮቹ እጅ የነበረውን ሂሳብ ለመተሳሰብ የፈለገን ንጉስ ትመስላለች›› በማለት ነው የሚጀምርልን። አገልጋዩ ዕዳውን ለመክፈል ባለመቻሉ ሊደረግበት የታዘዘው ነገር፤ እርሱ ራሱ፣ ሚስቱ፣ ልጆቹና ያለው ንብረት ሁሉ ተሸጦ ለእዳ ክፍያ እንዲውል ነበረ ጌታው ያዘዘው።
4. ባለእዳው እዳውን እንደሚከፍልና ጊዜ እንዲሰጠው ሲለምን እናያለን። ከእዳው ብዛት ጋራ ይህ ባሪያ በምንም መንገድ ያለበትን ይህንን አይነት እዳ ሊከፍል የሚችልበት ምንም መንገድ ሊኖር እንደማይችል አምናለሁ። ጌታው ግን እንዳዘነለትና እንደማረው ነው የምንመለከተው።
5. ሁለተኛው ተበዳሪ የነበረበት አጠቃላይ ሂሳብ 1600 ሳንቲም ወይም በአሜሪካ ሲታሰብ 16 ዶላር ነበረ። ከሁለተኛው አበዳሪ የማየው ነገር ሃይለኛ ጭካኔን ነው። ተመሳሳይነታቸው፡ ሁለቱም ዕዳ ነበረባቸው፣ ሁለቱም መክፈል አልቻሉም፣ ሁለቱም ጊዜ እንዲሰጣቸው እግር ስር ወድቀው ይለምናሉ፣ ልዩነታቸው ደግሞ፡ አንደኛው እዳው ጊዜ ቢሰጠውም መክፈል የማይቻል ሲሆን የሌላኛው መከፈል የሚችል አይነት እዳ ነበረ።
6. ጌታው አገልጋዩን ‹‹አንተ ክፉ አገልጋይ›› በማለት ነው የሚጠራው። እኔም ምህረት ጠይቀኸኝ እንደማርኩህ፣ አንተም ምህረት ስትጠየቅ ምህረት ልትሰጥ ይገባህ ነበረ በማለት ነው የነቀፈው። ጌታው ሲቆጣና ሲናደድ የሚታየው ባሪያው የተቀበለው አይነት ይቅርታ መስጠት እንቢ ሲል ነው።
7. በመጨረሻው ጥቅስ (ቁ35) ላይ ሊል የፈለገው ነገር ይቅርታን ከፈለጋችሁ ይቅር ማለት ይጠበቅባችኋል ለማለት ነው። እነዚህን ሁለት ጥቅሶች ደግሞ በአንድነት ስናስቀምጣቸው፤ ይቅርታ ማድረግ እንደሚጠበቅብን መረዳት ብቻ ሳይሆን፣ ለይቅርታችንም ገደብ ልናበጅለት እንደማይገባን ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች እንማራለን።
8. የመጀመሪያው አገልጋይ ከጌታው የተበደረው ብድር መጠኑ እጅግ ከፍተኛና በምንም ዓይነት ሊከፍለው የማይችለው እንደሆነ ስናይ፤ ሌላኛው ጓደኛው ከእርሱ የተበደረው ግን በቀላሉ ጊዜ ቢሰጠው መክፈል የሚችለው እንደነበረ እንረዳለን። የእነዚህ ሁለት ሰዎች ታሪክ ከእኛ ጋራ የሚመሳሰልበት፤ እግዚአብሔር እጅግ ብዙ የሆነውን ሃጥያታችንንና በደላችንን ይቅር ብሎን፣ እኛ ግን ወገኖቻችን አንዲት ነገር በእኛ ላይ ሲያደርጉብን ለዚያ ይቅርታ ማድረግ ትግል ይሆንብናል፤ በዚህ ሰዎቹን እንመስላቸዋለን ማለት ነው።

# ጥናት ስድስት ሉቃስ 14፡25-35 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ እየተናገረ ያለው እየተከተሉት ለነበሩት ‹‹ብዙ ህዝብ›› በማለት ሉቃስ ለሚናገራቸው ሰዎች ነው፡፡ የኢየሱስ ደቀ መዛሙር ሊሆን የማይችለው ሰው፤ አባትና እናቱን፣ ሚስትና ልጆቹን፣ ወንድምና እህቶቹን፣ እንዲሁም የራሱን ህይወት ጭምር የማይጠላ ሰው የእርሱ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይችልም፡፡ በተጨማሪም ደግሞ የራሱን መስቀል ተሸክም የማይከተለው ደቀ መዝሙሩ ሊሆን አይችልም፡፡
2. ኢየሱስ ይህንን ሲል አባት፣ እናት፣ ሚስት፣ ልጅ፣ ወንድም፣ እህት ሁሉ በጥላቻ እንድናያቸውን ከእነርሱ እንድንርቅ ማስተማሩ ሳይሆን፤ እኔ እንደምረዳው ለኢየሱስ ያለን ፍቅር ከማናቸውም ከምንወዳቸውና አቅርበን ከምናያቸው ሰዎች ሁሉ ሊበልጥ እንደሚገባው፤ ደግሞም ከኢየሱስና ከነዚህ ሁሉ አንድ ብቻ መምረጥ ቢኖርብን ምርጫችን ኢየሱስ ሊሆን እንደሚገባው ሲናገረን ነው ብዬ አምናለሁ፡፡
3. በኢየሱስ አመለካከት፤ ሕንጻን ለመስራት የሚፈልግ ሰው አስቀድሞ መውሰድ የሚኖርበት የመጀመሪያው እርምጃ ተቀምጦ ህንጻው የሚፈጅበትን ዋጋ መተመን እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ተቀምጦ ዋጋውን ሳይተምን ዝም ብሎ ማነጽ ቢጀምር፤ የተጀመረውን ቤት መጨረስ ባይችልና በመሃል ቢያቆም የሰዎች መሳለቂያ ይሆናል ብሎ ነው ኢየሱሰ የሚያስተምረው፡፡
4. ኢየሱስ ይህንን አነጋገር የተናገረው የእርሱ ደቀመዝሙር ለመሆን መጀመር መልካም ነገር እንዳልሆነ መናገሩ ሳይሆን፤ ጅማሬ ብቻ በቂ ሊሆን እንደማይችልና ደቀመዝሙርነት ሊያስከፍል የሚችለውን ነገር ሁሉ አመዛዝኖ መጀመር አስፈላጊ እንደሆነ ሲያሳስበን ነው፡፡
5. የነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ዋነኛ መልዕክት ‹‹ዋጋን መተመን›› ‹‹አስቀድሞ ማሰብ›› ‹‹ቅድመ ዝግጅት›› ‹‹አውቆ መግባት›› እና የመሳሰሉትን ሃሳቦች መሰንዘር ይቻላል፡፡
6. አስር ሺህ ሰራዊት ያለው ንጉስ ሃያ ሺህ ሰራዊት ያለውን ንጉስ መመከትና ማሸነፍ እንደማይችል ሳይሆን፤ ኢየሱስ ሊያስረዳን የፈለገው ይህንን ያህል ሰራዊት ያለውን የጦር ሃይል ለማሸነፍ የሚያስችል የጦር ሃይልም ሆነ ሥልት ወይም የተሻለ የጦር መሳሪያ እንዳለው እንደሌለው በደንብ ማውጣትና ማውረድ እንደሚኖርበት ሊያስተምረን ነው፡፡
7. ጨው መልካም ነው፣ ጨው ጣዕም ያለው ነገር ነው፣ ጨው ጣዕሙን ሊያጣ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ 5፡13 ላይ ‹‹እናንተ የምድር ጨው ናችሁ›› በማለት ለደቀመዛሙርቱ የተናገረውን በማስተያየት፤ ደቀመዝሙር ለዓለም ማጣፈጫና ማቆያ በሚሆን ህይወት እስከኖረ ድረስ መልካም እንደሆነ፤ ነገር ግን ይህንን ተግባሩን የማይወጣና ለራሱ ብቻ የሚኖር ከሆነ ጥቅም እንደሌለው እንረዳለን፡፡
8. ደህንነት ለእግዚአብሄር እንጂ ለሌላ ለማናችንም ምንም ዓይነት ነገር አላስከፈለንም፤ በአንጻሩ ግን ደቀመዝሙርነት የሚባለው ነገር፤ አለን የምንላቸውን ማናቸውንም ነገሮች ብቻ ሳይሆን ነፍሳችንንም ጭምር ለመስጠት ወስነን የምንገባበት ነገር እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

# ጥናት ሰባት ሉቃስ 10:1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ‹‹ሌሎች›› ሲል፤ ኢየሱስ እነዚህን ሰባ ሰዎች ሲልክ የመጀመሪያው እንዳልሆነና ከዚህ በፊት ሌሎች በዚሁ አይነት የላካቸው ሰዎች እንደነበሩ ሲጠቁመን ነው (ሉቃ 9:1-6)፡፡ የተላኩት ሰባ ሁለት ሰዎች ናቸው፣ ከነሱ በፊት የተላኩ ሌሎች ነበሩ፣ ሹመትን ሰጥቷቸዋል፣ የተላኩት እርሱ ሊሄድባቸው ወዳሰበት ከተሞች ነው፣ ሁለት ሁለት እያደረገ ነው የላካቸው፡፡ ቃሉ አንድ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል ስለሚል አንዱ ተስፋ ቢቆርጥ ሌላው እንዲያበረታው፣ አንዱ ቢያቅተው ሌላው እንዲደግፈው ይመስለኛል፡፡
2. ኢየሱስ ስለነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ለሰዎቹ የነገረው መከሩ ብዙ እንደሆነና ሰራተኞች ደግሞ ጥቂቶች እንደሆኑ ነው፡፡ ጥቂት ሰራተኞች በማለት የተናገረው በጊዜው ከእርሱ ጋራ ለመስራት የተነሱትን እነርሱንና አስቀድመው የተላኩትንም አስራ ሁለቱን ይጨምራል፡፡ ጌታ እንዲሳተፉ የፈለገባቸው ሁለት መንገዶች አያለሁ፤ እነዚህም የመከሩ ጌታ ሰራተኞችን እንዲልክ መለመንና፣ እነርሱም እንዲሄዱና በስራው እንዲሳተፉ ይፈልጋል፡፡
3. ኮረጆ፣ ከረጢት ወይም ጫማ እንዳይዙ፣ በመንገድ ላይ ለማንም ሰላምታ እንዳይሰጡ፣ ወደሰው ቤት ሲገቡ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን እንዲሉ፣ ያቀረቡላቸውን ሁሉ እየበሉና እየጠጡ እዚያው ቤት እንዲቀመጡ፣ ከአንድ ቤት ወደ ሌላው ቤት እንዳይዘዋወሩ፡፡ ኮረጆ፣ ከረጢት ወይም ጫማ አለመያዛቸው ለሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ በእርሱ እንዲታመኑ ሲሆን፤ በመንገድ ለማንም ሰላምታ አለመስጠት ደግሞ የሚያመለክተው የተልዕኮአቸውን አስቸኳይነት የሚጠቁም ሃሳብ ሊሆን እንደሚችል ይመስለኛል፡፡
4. የእነዚህ ሰዎች ዋነኛ ተልዕኮአቸው በሽተኞችን እየፈወሱ የእግዚአብሄር መንግስት ወደ እናንተ ቀርባለች በማለት ለህዝቡ መናገር ነበረ፡፡ መልዕክታቸውን ካልተቀበሉ ማድረግ የሚኖርባቸውንም ነገር ኢየሱስ ነግሯቸዋል፤ ይኸውም የእግራቸውን ትብያ አራግፈው ከዚያች ከተማ መውጣት ነው፡፡ ይህ አነጋገር የሚጠቁመን እናንተ ተቀበላችሁትም አልተቀበላችሁትም፤ የእግዚአብሄር መንግሥት ቀርባለች፤ የእናንተ እንቢተኛነት እውነቱን አይቀይረውም ማለት ነው፡፡
5. ኢየሱስ እነዚህን ከተሞች በማነጻጸር ማለት የፈለገው፤ በእነዚህ በአህዛብ ከተሞች ላይ እግዚአብሄር ፍርድ ከፈረደ፤ እነዚህ የጌታን ድንቅና ተአምራት አይተው፣ ትምህርቱን በግልጽ ሰምተው መልዕክቱንና መሲሁን በግልጽ ለመቀበል እንቢ ያሉ ከተሞች ከነዚያ ከአህዛብ ከተሞች የበለጠ ፍርድ ይጠብቃቸዋል ለማለት ነው፡፡
6. ክርስቶስ ከላካቸው ሰዎች የሚወጣው ቃል ልክ በክርስቶስ በራሱ እንደተነገረና እነርሱ የተናገሩትን መስማት እንቢ ካሉ ልክ የላካቸውን ኢየሱስ አልሰማም እንዳሉ እንደሚቆጠር ነው የምናነበው፡፡ አምባሳደሩን ከናቁትና የማይሰሙት ከሆነ ልክ የተላከበትን ሃገር እንደናቁ፤ አክብረው ከተቀበሉት ደግሞ የተላከበትን ሃገር እንዳከበሩ እንደሚቆጠር፤ በወንጌል መልዕክተኞችም ይህ እንደሚሰራ ነው ኢየሱስ እየነገራቸው ያለው፡፡
7. እነዚህ በደስታ የሚፈነድቁ ሰዎች ተልዕኮአቸው የተሳካ እንደነበረና አጋንንት እንኳን በስሙ እንደተገዙላቸው ነው ለኢየሱስ የነገሩት፡፡ እነርሱ ይህንን ሪፖርት ሲያመጡለት ኢየሱስ ደግሞ ዋነኛቸው የሆነው ሰይጣን ራሱ እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ እንዳየ ነገራቸው፡፡
8. በቁ19 ላይ የሰጠኋችሁ ሥልጣን እንዳለ ሆኖ፤ የደስታችሁ መሰረት ሊሆን የሚገባው ግን በአጋንንት መውጣት፣ በበሽተኛ መፈወስ ወይም ደግሞ እናንተ ለእኔ በምትሰሩት፣ በአገልግሎታችሁ ውጤትና በመሳሰለው ሳይሆን፤ እኔ ለእናንተ በሰራሁት ዘለዓለማዊ ሥራ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ያስፈልገዋል በማለት ነው አመለካከታቸውን ማስተካከል እንደሚኖርባቸው የተናገረው፡፡

<u>ጥናት ስምንት ዮሐ 21፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በመሪነት ደረጃ የምናየው ጴጥሮስን ሲሆን የነበሩት ተከታዮችም ቁጥር ከራሱ ጋራ ስድስት ነበሩ። ምንም ችሎታውና እውቀቱ ቢኖራቸው ያለ ኢየሱስ ምንም ማድረግ እንደማይቻል መማር ይችላሉ። ለእኛም በእውቀታችንና በማስተዋላችን ሳንመካ በእርሱ መታመን እንደሚኖርብን መማር እንችላለን።
2. ኢየሱስ ያዘዛቸው ትዕዛዝ መረባቸውን ከጀልባው ወደ ቀኝ እንዲጥሉ ነው። የማያውቁትን ሰው ትዕዛዝ ለመስማትና ለመታዘዝ ክፍት የሆኑበት ምክንያት እኔ እንደሚመስለኝ ቢሰሙትና ቢያደርጉት የሚጎድልባቸው ነገር ስለሌለ፤ እንደተባለው ከሆነ ግን ማትረፊያ እንደሚሆንላቸው በማሰብ ተስፋ በቆረጠ መንገድ ያደረጉት ይመስለኛል፤ ምክንያቱም ሌሊቱን ሁሉ የሚያውቁትን የዘዴ ዓይነት ሳይጠቀሙ ስላልቀሩ መሞከር የሚችሉት ነገር ስላለቀባቸው ነው ።
3. በሉቃስ 5፡4-11 ኢየሱስ ይህንኑ የመሰለ ተመሳሳይ ተአምር ያሳያቸው በመሆኑና ያንን በማስታወስ ይመስለኛል ወደዚህ አነጋገር የደረሰው። አሳ የሚያጠምዱበት መረብ ምንም ያህል አሳ ቢይዝ አለመቀደዱ፤ በእኛም አገልግሎት ወንጌላችን ምንም ያህል ነፍሳትን ብንይዝበትና ምን ያህልም ብንጠቀምበት የማይደክምና ሃይሉ የማይከሽፍ ብርቱ መሳሪያ መሆኑን መማር እንችላለን።
4. ተስፋ የቆረጡ ወይም ሞራላቸው የወደቀበት ሁኔታ ውስጥ ነበሩ።ኢየሱስ በዚህ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ የተናገራቸው አንድ ነገር ‹‹ኑ ቁርስ ብሉ›› የሚል ነበረ። ይህንን ካላቸው በኋላ ጌታ ያደረገው ነገር እንጀራውንና አሳውን እንዲመገቡ ሲሰጣቸው እንመለከታለን። እነዚህን የዛሉና የደከሙ ደቀመዛሙርት መግቦ ያበረታ ጌታ እኔም በመንፈሴ ስደክምና ስዝል እንደሚመግበኝና እንደሚያበረታኝ ተስፋ ሆኖልኛል።
5. የኢየሱስ ጥያቄዎችና የጴጥሮስም መልሰሶች ያተኮሩት በፍቅር ላይ ሲሆን፤ ከጴጥሮስ መልስ አስከትሎ ኢየሱስ የተናገራቸው ሃሳቦችም ትኩረታቸው ሃላፊነትን ወይም አገልግሎት ላይ ያተኮሩ ነበሩ። እግዚአብሄር ሃላፊነት ሲሰጥ ለእርሱ ካለን ፍቅር ተነስተን እንድናገለግለው እንጂ ግዴታን ከመወጣት ተነስተን የምናደርገው እንዳይሆን የሚያስተምረን ሲሆን፤ ፍቅርንና አገልግሎትን መነጣጠል አይቻልም።
6. እነዚህ ሁለት ክፍሎች የሚመሳሰሉትና የሚያስተምሩን አንድ እውነት ቢኖር እግዚአብሄርን ለማክበር አማኝ በህይወቱ ብቻ ሳይሆን በሞቱም እግዚአብሄርን ማክበር እንደሚችል ከሁለቱም ጥቅሶች መማር እንችላለን።
7. ይህ አይነቱ ወሬ የተነሳው ኢየሱስ ለጴጥሮስ ጥያቄ ከሰጠው መልስ ነው። ይህ ችግር በቤተክርስትያን አካባቢም በብዙ የሚታይና ብዙ ችግር የሚፈጥር ነው፤ ለዚህም መፍትሄ የሚሆን የሚመስለኝ ነገሩ ካልገባን የተናገረውን ሰው ይህንን ስትል ምን ማለትህ ነው ብለን ብንጠይቅና ለሌላ ከማስተላለፋችን በፊት ነገሩን እንደተረዳነውና እኛ እንዳሰብነው መሆኑን ማረጋገጥ ይረዳል እላለሁ እንችላለን።
8. ጴጥሮስ በተጨማሪ ማወቅ የፈለገው ነገር የዮሐንስ መጨረሻ ምን እንደሚሆን ማወቅ ነበረ።

# ጥናት ዘጠኝ ማቴ 28፡1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ ሴቶች የሄዱበት ወቅት፡ ሰንበት ካለፈ በኋላ፣ በሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን፣ ጎህ ሲቀድ ማለትም በማለዳ እንደሆነ እናነባለን። እነዚህ ሁለት ማርያሞች ጌታ ወደተቀበረበት መቃብር በዚያ ሌሊት ተነስተው የሄዱበትን ምክንያት ማቴዎስ በግልጽ ባይነግረንም እንኳን፤ ማርቆስ በ16፡1 ላይ፣ ሉቃስ ደግሞ በ24፡1 ላይ ገልጸውት እናያለን፤ ይኸውም ሬሳውን ሽቱ ለመቀባት እንደሆነ እናነባለን።
2. እነዚያ ጠባቂዎች ኢየሱስን የሚፈልጉ ሳይሆኑ ከኢየሱስ ገዳዮች ጋራ ተስማምተው የሚኖሩና ለኢየሱስ መሞት ግድ የሌላቸው ሲሆኑ፤ ሴቶቹ ግን የተሰቀለውን ኢየሱስን የሚፈልጉና በሶስተኛው ቀን እንደሚነሳ የተናገረውን አምነው በመቀበል ወደ መቃብሩ የመጡ ስለሆነ ነው እግዚአብሄር መልአኩን የላከላቸው። ጌታ በዚያ እንደሌለና እንደተናገረው እንደተነሳ ሲነግራቸው፤ ያዘዛቸውም ሄደው ለደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ከሙታን እንደተነሳና ወደ ገሊላ እንደሚቀድማቸው በዚያም እንደሚያገኙት እንዲነግሯቸው ነው።
3. ሁለቱ ስሜቶች ፍርሃትና ደስታ ናቸው። የፈሩበት ምክንያት የምድር መናወጥ መከሰቱና የጌታ መልዓክ በመገለጡ ሲሆን፤ የደስታ ስሜቱ ደግሞ የመጣው፣ ጌታቸው ከሙታን እንደሚነሳ የነገራቸው ነገር እውን መሆኑ በመልአኩ ስለተነገራቸው ነው።
4. ኢየሱስ እንደ መልአኩ ደቀ መዛሙርቴ ማለት ሲችል፤ ‹‹ወንድሞቼ› በማለት ነው የጠራቸው። ከዚህ የምማረው፤ እንደ ማር 3፡34 በመሳሰሉ ስፍራዎች ደቀመዛሙርቱን ወንድሞቼ ያላቸው ጌታ ጥፋታችንንና ጉድለታችንን ወይም ያለንበትን ሁኔታ አይቶ እንደማይቀያየርና ሁልጊዜ ፍቅሩ ያው እንደሆነ እረዳለሁ።
5. እኔን ያስገረመኝ ሁለት ነገር ነው፤ የመጀመሪያው ጠባቂዎቹ በአይናቸው ፊት የተከናወነውን ሁኔታ ሁሉ ተመልክተው እያሉ እውነቱን ለማወቅ ከመሞከር ይልቅ በገንዘብ ራሳቸውን ለመሸጥ መወሰናቸው ሲኖን፤ ሌላው ደግሞ የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ይህንን የመሰለ ምስክርነት ከራሳቸው ሰዎች እየሰሙ ነገር ግን ከማመን ይልቅ ነገሩን ለመሸፈን መሞከራቸው ጌታ ዓይንን ካልከፈተ በቀር ተአምራት የሰውን ልብ ጥንካሬ ሊቀይር እንደማይችል እረዳለሁ።
6. ደቀመዛሙርቱ በመጀመሪያ ያደረጉት ኢየሱስ ወዳመለከታቸው ቦታ መሄድ ነው፤ ሌላው ደግሞ ኢየሱስን ባዩት ጊዜ እንደሰገዱለት እናነባለን። በደቀመዛሙርቱ መሃል ሌላ የተከሰተ ነገር የምናነበው አንዳንዶቹ እንደተጠራጠሩ ማቴዎስ ይነግረናል።
7. ደቀመዛሙርቱ ተልዕኳቸውን እንዲወጡ ከኢየሱስ አገኙ የምለው ነገር፤ በአንደኛ ደረጃ ‹‹ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል›› በማለት ሁሉ ነገር ከእርሱ ስር እንደሆነና የሚያስፈራቸው ነገር ሊኖር እንደማይችል፣ በተጨማሪ ደግሞ በቁ20 መጨረሻ ላይ ወንጌሉን ለመሰራጨት በሚሄዱበት ሁሉ እርሱ ሁልጊዜ ከእነርሱ እንደማይለይ መናገሩ ለነርሱ የሚያበረታታና ተስፋ የሚሰጥ ነገር ነው ብዬ አምናለሁ።
8. እነዚህ አንዳንዶቹ ተጠራጣሪዎች ሲሆኑ፣ በማርቆስ ወንጌል ላይ የምናያቸው ደግሞ እምነት የጎደላቸውና፣ የልብ ድንዳኔ የያዛቸው ሰዎች ናቸው።